ያልገባቸው አይሁድ በበአለ ሃምሳ ዕለት “ይህ ምንድነው?” ብለው የጠየቁት የመንፈስ ቅዱስ ሙላት አይነተኛ ምልክት የሆነው ልሳን ዛሬም ለአንዳንዶች ጥያቄ ሊሆን ይችላል።

# በልሳን ለምን እንጸልያለን?

## የመንፈስ ቅዱስ ሙላት አይነተኛ ምልክት በልሳን መናገር ነው!

ፓስተር አስፋው በቀለ

# ልሳን መጽሐፍ ቅዱስ ነውን?

**“በልሳን መናገር”!** የሚለውን ቃል ገና ከመንፈስ ቅዱስ አማኞች አንደበት ሲወጣ በአማኞችም ሆነ በማያምኑ መካከል የተለያየ አመለካከቶች ይፈጠራሉ። በልሳን መናገርን የሚደግፉም ሆነ የሚቃወሙ ብዙ መጣጥፎች በየስፍራው ይገኛሉ። አንዳንዶች “በልሳን መናገር አሁን በዚህ ዘመን ላለነው አማኞች የተሰጠ አይደለም” ብለው ይከዳሉ።

ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ እንደምንመለከተው በልሳን መጸለይ *(**glossolalia**)* በመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን ይዘወተር የነበረና ከጊዜ በኋላ ግን ቤተ ክርስቲያን በመካከለኛው ዘመን ወደ መንፈሳዊ ጨለማ ውስጥ ስትገባ የተዳፈነ እንጂ፤ ፈጽሞ ልሳን የቀረ ነገር አልነበረም። አስገራሚው ነገር ግን በልሳን መጸለይ ቀርቷል የሚሉት ወገኖች በመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ማመናቸው ነው። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ከዶ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎችን ማመን ስር የለቀቀና የተዘባረቀ የስነ መለኮት መረዳት ምልክት ነው።

## ለመሆኑ በልሳን ለምን እንናገራለን?

*ማር.16፡15-17* ***[15]እንዲህም አላቸው፤ ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፤ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ፤ [16]ያመነ የተጠመቀ ይድናል፤ ያላመነ ግን ይፈረድበታል:: [17]የሚያምኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል፤ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፤ በአዲስ ልሳንም ይናገራሉ፤ [18]እባቦችን በእጃቸው ይይዛሉ፤ የሚገድል መርዝ ቢጠጡ እንኳ አይጎዳቸውም፤ እጃቸውንም በሕመምተኞች ላይ ይጭናሉ፤ እነርሱም ይፈወሳሉ::***

በዚህ ጥቅስ እንደምንመለከተው ወደ ዓለም ሁሉ ሄደው ወንጌልን እንዲሰብኩ ያዘዛቸው ጌታ ኢየሱስ በልሳን መናገር ወደ አለም ሁሉ የተላኩት የአማኞች አንዱ ምልክት እንደሆነ ይናገራል።

1. በልሳን መናገር አስፈላጊ ሆነ ለሚለው ጥያቄ ምላሻችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ በልሳን መናገርን ስላበረታታ **(endorsed)** ነው::”

**የሐዋርያትን መልዕክት ከፍተን ስለመንፈስ ቅዱስ ሙላት/ጥምቀትና ወዲያውኑ ለጥቆም ሙላቱን የሚጠቁመው ልሳን መሆኑን የሚከተሉትን ሦስት ጥቅሶች በመመልከት እንመርምር . . . ይህም ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት ማስረጃ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ንድፍ ነው።**

***ሐዋ.***1:4-5; 2:1-4, ***[4]ከእነርሱም ጋር በማእድ ተቀምጦ ሳለ እንዲህ ሲል አዘዛቸው፤ ከኢየሩሳሌም አትውጡ፤ ነገር ግን እኔ ስናገር የሰማችሁትን፣ አብ የሰጠውን ተስፋ ጠብቁ፤ [5]ዮሐንስ በውሃ አጥምቆ ነበርና፣ እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ::....*** [2:1] ***የበዓለ ኀምሳ ቀን በደረሰ ጊዜ ሁሉም በአንድነት፣ በአንድ ስፍራ ተሰብስበው ነበር፤ [2]ድንገትም እንደ ብርቱ ዐውሎ ነፋስ ያለ ድምፅ ከሰማይ መጥቶ ተቀምጠው የነበሩበትን ቤት እንዳለ ሞላው:: [3]የእሳት ምላሶች የሚመስሉም ታዩአቸው፤ ተከፋፍለውም በእያንዳንዳቸው ላይ ዐረፉ:: [4]ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፤ መንፈስም እንዲናገሩ በሰጣቸው መጠን በሌሎች ቋንቋዎች ይናገሩ ጀመር::***

ሐዋርያት 1፡5 ና 2፡4ን ስናነጻጽር በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅና በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ለአንድ ልምምድ በተለያየ ጊዜ የተሰጡ ስሞች (**synonyms**) ናቸው። ይህኑን አይነት ተመሳሳይ አሳብ በቁጥር 10 እና 19 ላይ እንመለከታለን።

*ሐዋ.10:44-47* ***[44]ጴጥሮስ ይህን እየተናገረ ሳለ፣ ቃሉን በሰሙት ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው:: [45]ከጴጥሮስ ጋር የመጡት፣ ከተገረዙት ወገን የሆኑት አማኞች፣ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በአሕዛብም ላይ ደግሞ መፍሰሱን ሲያዩ ተገረሙ፤ [46]ይኸውም በልሳን° ሲናገሩና እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ ስለሰሟቸው ነው:: በዚያ ጊዜ ጴጥሮስ እንዲህ አለ፤ 47 እነዚህ ሰዎች እንደእኛ መንፈስ ቅዱስን ስለተቀበሉ፣እንግዲህ በውሃ እንዳይጠመቁ የሚከለክላቸው ማን ነው?***

በቆርኖሌዎስ ቤትም ጴጥሮስ ለመጀመሪያ ጊዜ በአህዛብ መካከል ወንጌል በሰበከ ጊዜ ይሰሙት በነበሩት ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ እንደሞላባቸውና የመንፈስ ቅዱስ ሙላታቸውም ምልክት **ልሳን** እንደነበረ ከሐዋ.2፡46 እናነባለን።

በሐዋርያት ስራ ምዕራፍ 1 እና 2 አማኞች በመንፈስ ቅዱስ ሲጠመቁ ወይንም በመንፈስ ቅዱስ ሲሞሉ ተመልክተናል። በሐዋርያት 10 ደግሞ ጴጥሮስ እነዚህ አህዛብ ልክ እንደ በዓለ-ኀምሳው ቀን ሐዋርያት የተቀበሉትን ያንኑ መንፈስ እንጂ ሌላ መንፈስ እንዳልተቀበሉ ይመሰክራል (ቁ.47)። በተጨማሪም በዚህ ልምምድ (ልሳን) መንፈስ ቅዱስን እንደተቀበሉ ማስረጃ አድርጎ ያቀርባል።

ሐዋርያት ስራ 19፡4-6 [4] *ጳውሎስም፣ የዮሐንስ ጥምቀትማ የንስሓ ጥምቀት ነበር፤ ዮሐንስም ራሱ ሰዎች ከእርሱ በኋላ በሚመጣው በኢየሱስ እንዲያምኑ ተናግሮአል አላቸው:: [5]እነርሱም ይህን በሰሙ ጊዜ በጌታ በኢየሱስ ስም ተጠመቁ:: [6]ጳውሎስም እጁን በላያቸው በጫነ ጊዜ፣ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው፤ በሌሎች ቋንቋዎች[ т ] ተናገሩ፤ ትንቢትም ተናገሩ:: [7]ሰዎቹም በአጠቃላይ ዐሥራ ሁለት ያህል ነበሩ::*

2. እነዚህ ከላይ ከሐዋርያት ስራ 2፣10ና 19 የጠቀስናቸው ሦስት ምሳሌዎች በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት አይነተኛ ምልክቱ ልሳን መሆኑን በእግዚአብሔር ቃል ምስክሮች ናቸው።

ሐዋ.19፡1-3 ደግሞ - *አጵሎስ በቆሮንቶስ በነበረበት ጊዜ፣ ጳውሎስ በላይኛው አገር ዐልፎ ወደ ኤፌሶን መጣ፤ በዚያም አንዳንድ ደቀ መዛሙርትን አግኝቶ [2]ባመናችሁ[ f ] ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን? አላቸው:: እነርሱም፣ አልተቀበልንም፤ እንዲያውም መንፈስ ቅዱስ መኖሩን እንኳ አልሰማንም አሉት:: [3]ጳውሎስም፣ ታዲያ፣ በምን ተጠመቃችሁ? አላቸው:: እነርሱም፣ የዮሐንስን ጥምቀት አሉት::”*

እነዚህ የዳኑ አማኖች ቢሆኑም ገና በመንፈስ ቅዱስ አልተሞሉም፤ መንፈስ ቅዱስም ማንና ምን እንደሚሰራ አያውቁም። ጳውሎስም መጥቶ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን አስተዋወቃቸው። ስለዚህ ሰው ክርስቶስን አዳኝ አድርጎ በተቀበለ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ ተወለደ እንጂ በመንፈስ ቅዱስ ተጠመቀ ማለት እንዳልሆነ በግልጥ ያስረዳናል።

በመጠቅለልም፤ ከላይ የተመለከትናቸው የሃዋ.2፣10ና 19 ትክክለኛ የሆነን ቅደም ተከተሎች ያስተምሩናል፡

- *የውሃ ጥምቀትና የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የተለያየ ነው።*
- *በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቁ አማኞች የሙላቱን ማስረጃ በልሳን ይናገራሉ።*

ሐዋ 2:4 [4]*ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፤ መንፈስም እንዲናገሩ በሰጣቸው መጠን በሌሎች ቋንቋዎች[ ሐ ] ይናገሩ ጀመር::*

❖ *በልሳን ለምን እንናገራለን? — ራስችን ለመንፈስ ቅዱስ መሪነት፣ አለቅነትና ብቃት እንድንሰጥ እድል ይሰጠናል። ልሳን በትህትናና በፈቃዳችን አንደበታችንን ለመንፈስ ቅዱስ ስናስማርክ ያለምንም ችግር ከተሞላው ቅባት ኮለል ብሎ ይተረተራል።*

ሐዋ. 11:15-18,15፤ *እኔም ገና መናገር ስጀምር፣ መንፈስ ቅዱስ፣ በመጀመሪያ በእኛ ላይ እንደ ወረደ ሁሉ በእነርሱም ላይ ወረደ:: [16]በዚህ ጊዜ፣ ዮሐንስ በውሃ አጠመቀ፤ እናንተ ግን በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ ሲል ጌታ የተናገረው ቃል ትዝ አለኝ:: [17]እንግዲህ እግዚአብሔር በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስናምን ለእኛ የሰጠንን ስጦታ ለእነርሱም ከሰጣቸው፣ ታዲያ፣ እግዚአብሔርን መቋቋም እችል ዘንድ እኔ ማን ነኝ?[18]ይህን በሰሙ ጊዜም የሚሉትን አጥተው እንዲህ እያሉ እግዚአብሔርን አመሰገኑ፤ ይህማ ከሆነ፣ አሕዛብም ወደ ሕይወት ይመጡ ዘንድ፣ እግዚአብሔር ንስሓን ሰጥቷቸዋል ማለት ነዋ::*

❖ *ልሳን በተናጋሪው ህይወት ውስጥ የእግዚአብሄርን ዕውንነት ስለሚያረጋግጥ*

ሐዋርያት ከአይሁድ ውጪ ወደ አህዛብ ሄደው ወንጌል መናገር ይኑርባቸው ወይ አይኑርባቸው ገና የተገለጠ መረዳት በሌላቸው ጊዜ ጴጥሮስ በቆርኔሌዎስ ቤት ገብቶ የገጠመውን አስገራሚ መለኮታዊ ልምምድ ለሃዋርያት ሲተርክላቸው፤ ሃዋርያትም የመንፈስ ቅዱስ መውረድና የልሳናቱን ምልክት ነገር ሲሰሙ፤ እግዚአብሄር ለአህዛብም የደህንነት እቅድ እንዳለው እንዲረዱ አደረጋቸው። የአህዛብም በልሳን መጻለይ ለሃዋርያት ጸረ-አህዛብ የሆነ አመለካከታቸውን እንዲለውጡ አስገድዷቸዋል።

*ሐዋ.19:2a,6* [2]***ባመናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን? አላቸው:: እነርሱም፣ አልተቀበልንም፤ እንዲያውም መንፈስ ቅዱስ መኖሩን እንኳ አልሰማንም አሉት::. . .*** [6]***ጳውሎስም እጁን በላያቸው በጫነ ጊዜ፣ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው፤ በሌሎች ቋንቋዎች[7] ተናገሩ፤ ትንቢትም ተናገሩ::***

*❖የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለሌሎች የጸጋ ስጦታዎች በርን ይከፍታል። በቁ.6 ላይ "ትንቢትንም ተናገሩ" ይላል።*

ጌታ ኢየሱስ የተጸነሰው በመንፈስ ቅዱስ (ማቴ. 1:20) ነበር። ነገር ግን የ30 አመት ሲሆነው በዮርዳኖስ ወንዝ በውሃ ሲጠመቅ በመንፈስ ቅዱስ ኃይልም ተቀባ (ዮሐ.1:32-33 . . . ሐዋ.10:38). ከዚህም የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ልምምድ በኋላ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በቃና ዘገሊላ የመጀመሪያውን ተዓምራት አደረገ (ዮሐ. 2:11).

በመንፈስ ቅዱስ ሙላት ውስጥ የሚለቀቀው ጸጋ የመንፈስ ቅዱስ ቅብዓት ነው። ይህም አማኝን ከፍ ወዳለ የህይወት ልምምድ ያሸጋግረዋል።

*1ቆሮ.12፡7፤10* [7]***ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ሰው የሚሰጠው ለጋራ ጥቅም ነው:: …*** *[10]* [10]***ለአንዱ ታምራትን የማድረግ፣ ለሌላው ትንቢትን የመናገር፣ ለሌላው ደግሞ መናፍስትን የመለየት፣ ለአንዱ በልዩ ልዩ ልሳን የመናገር፣ ለሌላው ደግሞ በልዩ ልዩ ልሳን[7] የተነገረውን የመተርጐም ስጦታ ይሰጠዋል::.***

❖ ጥምር የመንፈስ ቅድስ ስጦታዎች — ልዩ ልሳንና ትርጉም ስጦታ — በቤተ ክርስቲያን አምልኮ ውስጥ አብረው ይገለጣሉ። ለመንጋው ጥቅም *1ቆሮ.14፡2*

*❖በልሳን መጸለይ በመንፈስ ቅዱስ ውስጥ ሆኖ ወይንም ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ሆኖ መጸለይ ማለት ነው።* ***praying "in" or "with the spirit."*** በተወለድንበት ቋንቋ ስንጸልይ በአእምሮአችን እየጸለይን ሲሆን በልሳን ስንጸልይ ደግሞ በመንፈስ መጸለያችን ነው።

*1ቆሮ. 14:4* *በመንፈስ የሚጸልይ* ***ራሱን ያንጻል፤*** *ትንቢትን የሚናገር ግን ቤተ ክርስቲይንን ያንጻል።*

3. *በልሳን የሚናገር ይታነጻል።* ***edified, built up.*** አንዳንዶች ይህንን ጥቅስ አዛብተው ስለሚረዱት የልሳንን ጠቃሚነት አቅልለው ይመለከቱታል።

ጳውሎስ የሚናገረው፡-

(1) በልሳን መናገር ተናጋሪውን ያንጻል (2) በቤተ ክርስቲያን የሚነገር ትንቢት ጉባኤን ያንጻል። በዚህም መሰረት ልሳንም ትንቢትም ያንጻልም።

***ለምን በልሳን?*** *— ታላቁ የአዲስ ኪዳን ሃዋርያ ጳውሎስ ስለዚህ ስጦታ በታላቅ ክብር ተናግሯል፤ በሚያሳዝን ሁኔታ ግን ልሳን ከብዙ አብያተ ክርስቲያናት የተከለከለ ወይንም የማይሰበክ ጉዳይ ነው።*

- *1ቆሮ.14:5a, 39 "ሁላችሁም በልሳን እንድትጸልዩ እወዳለሁ....በልሳን ከመናገር አትከልከሉ"*

***ለምን በልሳን?*** *— የልሳን ስጦታ (1ቆሮ.12:10)፤ ከልሳን መተርጎም ስጦታ ጋር ሲጎዳኝ ቤተ ክርስቲያን ትታነጻለች (1ቆሮ.12:10)*

- ትንቢት የሚናገር ልሳን ከሚናገር ይበልጣል ማለቱ፤ ስጦታዎቹን ማወዳደሩ ሳይሆን በሰው ህይወት ላይ የሚያመጣውን መንፈሳዊ ለውጥና ፍሬን በማየት ነው።
- *1ቆሮ. 14:14-15 - በልሳን የሚጸልይ ሰው በመንፈሱ እየጸለየ ነው።*

***ለምን በልሳን?*** *በጸሎት ህይወታችን ሚዛናዊ እንድንሆንና ሚዛናዊ የሆነ አምልኮ እንድንለማመድ ያደርገናል።*

- ጳውሎስ በመንፈስ መጸለይና በአዕምሮ መጸለይን ያበረታታል።በዚሁም ክፍል ጳውሎስ በመንፈስና በ አዕምሮ መዘመርን ያስተምራል። *1ቆሮ. 14:16-17*

***ለምን በልሳን?*** — *በልሳን ስንጸልይ "መልካም አድርገን እንድንባርከው ያደርገናል።"*_ በሃዋ.2:4 እንደተጠቀሰው ልሳን በመንፈስ ቅዱስ መነዳት የምንናገረው ቋንቋ ነው። ተናጋሪው የንግግሩን ይዘት ላይረዳ ይችላል፤ እግዚአብአብሔር ግን ያውቀዋል።

- *ከሁላችሁ ይልቅ በልሳናት እናገራለሁ......1ቆሮ. 14:18*

***ለምን በልሳን?***_— *ሃዋርያዊ ልምምድ ስለሆነ....* ጳውሎስ በልሳን ጸልዩአል፤ በበዓለ ሃምሳ ቀን የኢየሱስ 12ቱ ሃዋርያት በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው በልዩ ልሳናት ጸልየዋል (ሃዋ. 2:1-4) *1ቆሮ. 14:26*

ሃዋርያው ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን የሚያንጹ ብሎ የጠቀሳቸው አንዱ የጸጋ ስጦታዎች በተለይም ልሳን፣ትርጉምና ትንቢት ናቸው። አምልኮን እየተለማመድን ልሳናትን መቃወም አንችልም፤ አብንና ወልድን ያለምንም ጥርጥር እየተቀበልን መንፈስ ቅዱስንና ስጦታውን መግፋት አንችልም። መንፈስ ቅዱስ ቃል፣ አምልኮና ስጦታዎችን የሚሰጠን ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽና ለጥቅም ነው።

◈ ***"አዲስ** ልሳናት"* (ማርቆስ 16:17)፤ ◈ ***"ሌሎች** ልሳናት"* (ሐዋ. 2:4)፤*"ልዩ አይነት (**kinds**) ልሳናት"* (1ቆሮ.12:10, 28)፤ ***ልዩ ልዩ (diversities)*** *ልሳናት"* (1ቆሮ.12:28)፤ *"የስውና የመላእክት ልሳናት"* (1ቆሮ.13:31) ይህም የሰው ቋንቋና ሰማያዊ ወይንም የመላእክት ቋንቋ ነው፤ *"የማይታወቅ ልሳን (**unknown**)... ማንም ሰው ሊረዳው የማይችለው"* (1ቆሮ.14:2)።

ለማጠቃለል ያህል:- ቅዱሳን ለምን በልሳናት እንዲጸልዩ እናበረታታለንን? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ እንሞክር:-

1. **ኢየሱስ ክርስቶስ** እውነተኛ አማኞች በልሳን እንደሚናገሩ ስለተናገረ (ማር.16:17).
2. ልሳን አንድ ሰው በመንፈስ ቅዱስ የመሞላቱ ምልክት (**evidence**) ስለሆነ (ሐዋ. 1:5፤ 2:1-4፤ 10:44-46፤ 11:15-17፤ 19:1-6).
3. በልሳን መናገር በመንፈስ ቅዱስ ለመመራት የተመቻቸ መንገድ ስለሚከፍት (ሐዋ. 2:4).
4. ልሳን በአማኙ ህይወት ውስጥ እግዚአብሔር ህያው እንደሆነ ስለሚገልጥ (ሐዋ. 11:15-18).
5. በልሳን በመጸለይ የተረጋገጠ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ለመንፈስ ቅዱስ ሌሎች ስጦታዎች አይነተኛ በርን ስለሚከፍት (ሐዋ.19:2,6).
6. ልሳናት ከነትርጉማቸው ለቤተ ክርስቲያን የጋራ ጥቅም ስላላቸው (1ቆሮ. 12:7, 10).
7. በልሳን መናገር ለእግዚአብሔር መናገር ስለሆነ (1ቆሮ.14:2).
8. በልሳን *መጸለይ በመንፈስ "in" ወይንም "with the Spirit" መጸለይ ስለሆነ* (1ቆሮ. 14:2, 14-15).
9. በልሳን የሚናገር ሰው የታነጸ (**edified**) ስለሚሆን (1ቆሮ.14:4).
10. ሐዋርያው ጳውሎስ በልሳን መናገርን በግልጥ ይደግፍ ስለነበር (1ቆሮ.14:5, 39).
11. ልሳን ሲተረጎም ቤተ ክርስቲያንን የሚያንጽ ስለሆነ (1ቆሮ.14:5, 12-13).
12. በልሳን በመንፈስም ሆነ በአዕምሮ ስንጸልይ ሚዛናዊ የሆነ የጸሎትና የአምልኮ ህይወት ስለሚሰጠን፤ (1ቆሮ.14:14-15).
13. በልሳን ስንጸልይ የሚገባው ምስጋና በትክክለኛው መንገድ ለእግዚአብሔር የሚገባውን ማቅረብ ስለሚያስችለን (1ቆሮ.14:16-17).
14. ልሳን መናገር የክርስቶስ ሃዋርያትም ልምምድ ስለነበረ (1ቆሮ.14:18 እና በበዓለ ኀምሳ).
15. 1ቆሮ.14፡5 ***"ሁላችሁ** በልሳናት እንድትናገሩ እወዳለሁ"*

# የጸጋ ስጦታዎች

በድምጽ የሚገለጡ ስጦታዎች

1. ልሳን = በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በማያውቁት ቋንቋ መናገር
2. ትርጉም = በማይታወቅ ልሳን የተነገረውን ሰው ወደሚረዳው ቋንቋ መተርጎም
3. ትንቢት = በመንፈስ መነዳት ጉባዔን የሚመክርና የሚያንጽን ቃል መናገር፤ማነጽ

1. የልሳን መናገር ስጦታ አይነቶች - 1ቆሮ.12፡10 "....ለአንዱም በልዩ አይነት ልሳን መናገር..."

- ልሳን
    - ✓ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት አይነተኛ ምልክት ነው - በመንፈስ ቅዱስ ሙላት ሐዋ.2፡4፤ 10፡44-46፤ 19፡16-17
    - ✓ ይህ ጥምቀት ወደ መለኮታዊ ልምምድ
    - ✓ በጸሎት መንፈስ ሆነን ከእ/ር ጋር የምንነጋገርበት ቋንቋ
    - ✓ ተሞልተው የማይናገሩ ጥቂት ሰዎች ነበሩ ------ ዝሆን ኩምቢ ባይኖረው

- ልዩ አይነት (የማታወቅ) ልሳናት =
    - ✓ ሳያዘወትር የሚመጣ ነው
        - ለማያምኑ ምልክት ነው - 1ቆሮ.14፡21-22፤ሃዋ.2፡7-8፤11፤ ኢሳ.28፡11-12
        - ውጤቱ =ሰዎች ይለወጣሉ፤
    - ✓ አዘውትሮ ሲመጣ
        - 1ቆሮ.14፡2፤4 = አዘውትሮ በልሳን የሚጸልይ
            - ለእግዚአብሔር ይናገራል
            - ምስጢርን (ሰው በአዕምሮው ሊረዳው አይችልም)
            - ራሱን ያንጻል

| የማታወቅ ልሳን | ትንቢት |
|---|---|
| ለእ/ር ይናገራል | ለሰው ይናገራል |
| ሰው የማይረዳው | ሰው የሚረዳው ነው |
| ራሱን ያንጻል | ቤ/ክንን ያንጻል |

- ያልተተረጎመ ልሳን =

1ቆሮ.14፡14 = የአማኝ መንፈስ ቀጥታ ወደ እ/ር ሲጸልይ አዕምሮው ያለፍሬ ነው።

1ቆሮ.2፡11-15፤ 16-17 = መንፈስ የሰው የውስጠኛው ክፍል ሆኖ ከጌታ ጋር ቀጥታ መነጋገር የሚችል ነው፤ መንፈስ ለመንፈስ ይናገራል፤ ዕብ.4፡12

ዮሃ.7፡38፤ ኢዮብ32፡8፤18-19፤ ምሳ.18፡8፤14 = የሰው መንፈስ አንዳንዴ ልብ፤ ውስጠኛ፤ ሆድ ተብሎ ይጠራል።

ምሳሌ.20፡27 = የሰው መንፈስ የእ/ር መብራት ነው። መዝ.51፡6

1ቆሮ.14፡15-16 = በማይታወቅ ልሳን መጸለይ አዕምሮን ያለፍሬ (መረዳት) ነው

ኤፌ.6፡18 = ሳናቋርጥ እንድንጸልይ ይረዳናል

ሮሜ.8፡26-27 = መንፈስ ቅዱስ በጸሎት ጊዜ መለኮታዊ ርዳታን ይሰጣል።

ይሁዳ 20-21 = ራስን በእ/ር ፍቅር እንድንጠብቅ ይረዳናል።

በልሳን ውስጥ የሚሰሩ ስራዎች፡-

1. ምስጋና = ለእ/ር
2. ምልጃ = ለሌሎች
3. ተግሳጽ = የጠላትን ስራ
4. የሚያንጽ = ለጉባዔ

- ✓ 1ቆሮ.12፡30 = በግል ልሳን የሚጸልዩ የጉባዔው አላቸው ማለት አይደለም
- ✓ 1ቆሮ.14፡18-19 = ከላይ የተጠቀሱት በስተቀር የግል ልሳን ማጉላቱ ጥቅም የለውም
- ✓ 1ቆሮ.14፡28 = በጉባዔ ለራስና ለ እ/ር ልሳን መናገር ይቻላል

ትርጉም

- ✓ ትርጁማን መሆን ማለት አይደለም
- ✓ በልሳን የተነገረውን በመንፈስ መረዳትና መግለጥ
- ✓ በልሳን የተነገረውን በሰው ቋንቋ ማሳለፍ
- ✓ ለጉባዔ መታነጽን ያመጣል
- ✓ ሲተረጎም- ረጅም/አጭል ሊሆን ይችላል
    - o ማኔ ቴቄል ፋሬስ
- ✓ ትክክለኛ ትርጉም ነው።

PASTOR ASFAW BEKELE

www.zionsglorychurch.com